# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ አጭር ታሪክ

*በአማኑኤል ተፈሪ ማሞ*

**መግቢያ**

ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ታሪክ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፣ ጥናቶች ተደርገዋል፣ እንዲሁም ፊልም ተሠርቷል። በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ሁሉንም ታሪክ ለመዘርዝር ባይቻልም፣ ጉልህ የሆኑት ለቤተ ክርስቲያኒቷ መመሥረት አስተዋጽዖ ያደረጉት ዐበይት ጉዳዮች የሚዳስሱ ይሆናሉ።

የፕሮቴስታንት እምነት ኢትዮጵያን ለመድረስ ያደረገው ጥረት ከ17ኛው ምእተ ዓመት ጀምሮ የነበረ ነው። በመጀመሪያ ከመጡት ሚስዮናውያን መካከል በ1634/5 የደረሰው ፒተር ሄይ ሊንግ እንዲሁም በ1830 ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘው ኢትዮጵያ የደረሱት ሳሙኤል ጎባትና ክርስቲያን ኩግለር ይገኙበታል።

**የሚስዮናውያን በኢትዮጵያ ሥራ መጀመር**

ከመቶ ስልሳ (160) ዓመት በፊት በጀርመንና ስዊድን ወንገላውያን ክርስቲያኖች ለኦሮሞ ሕዝብ ወንጌልን በማድረስ በዚያውም ደግሞ ኢትዮጵያን በሙሉ እና የአፍሪካን አኅጉር በወንጌል ለመድረስ በብርቱ እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር።

«ቸርች ሚሽነሪ ሶሳይቲ» የተባለ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ዋና ዓላማ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1824 ዓ.ም ያሳተመውን አራቱን ወንጌል፣ ከዚያም በ1840 ዓ.ም ያሳተመው ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ለሚያነቡ የሰሜን ኢትዮጵያ ሰዎች ማድረስ ነበር። በሌላ በኩል የአሜሪካ ፕሪስቢቴሪያን ሚስዮንም በ1921 ዓ.ም በኢሉባቡር፣ ጎሬ የወንጌል ሥራ የጀመሩ ሲሆን ዶክተር ቶማስ ላምቤ ከቀደምት ሚሲዮናዊያኑ አንጋፋው ነበሩ።

እንደ ጀርመንና ስዊድን ሚስዮናውያን ሁሉ የ «ቸርች ሚሽነሪ ሶሳይቲ» ዓላማ ወንጌል ሳይቀበል የቆየውንና «ጋላ» በመባል ይታወቅ የነበረውን የኦሮሞ ሕዝብ በወንጌል መድረስና በዚያውም የወንጌልን አገልግሎት በአፍሪካ አኅጉር ማስፋፋት ነበር።

ቄስ ዮሐን ሉድዊግ ክራፍ የተባለ ጀርመናዊ ካህን ለጥቂት ዓመታት በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፈቃድ አንኮበር እየኖረ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ የተቻለውን መረጃ መሰብሰብ ጀመረ። ጀርመን አገር ለነበሩ ወዳጆቹም ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ብዙ ጽሑፎችን በሪፖርት መልክ ስለላከላቸው በእንግሊዝና በስዊድን አገር ጭምር በመጽሔቶች ላይ በመታተማቸው የብዙ ሰዎችን አትኩሮት ማግኘት ጀመረ። ቄስ ዮሐን ሉድዊግ በጽሑፎቹና በሪፖርቶቹ የኦሮሞ ሕዝብ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ስለሆነ ወንጌል ቢሰበክለት እንደ ጀርመኖች ኃያል ሕዝብ ሊሆን እንደሚችል ይናገር ነበር።

ከዚህ የተነሣ በጀርመንና በስዊድን የነበሩ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ታላቁን የምሥራች ለኦሮሞ ሕዝብ ለማድረስ ራእዩ ከታያቸው ሰዎች መካከል አንዱ ቄስ ሉዊ ሐርምስ የተባለ በሀገሩና ሔርማንስቡርግ በተባለ መንደሩ እየተዘዋወረ የብዙ ሰዎችን ድጋፍ በማግኘቱ «የሔርማንስቡርግ ሚስዮን» በመባል የታወቀውን የሚስዮን ማኅበር በ1849 ዓ.ም. መሠረተ። ወደ መንፈሳዊ ተቋማት በመግባት ወደ

ኦሮሞ ሕዝብ ወንጌል ለማድረስም ሚስዮናውያን መሠልጠን ጀመሩ:: ከወንጌል ትምህርት በተጓዳኝ ሕዝቡን ዘመናዊ የእርሻ ዘዴ፣ አናጢነትና ግንበኝነት እንዲሁም ሌሎችን ሙያዎች ለማስተማር የሚመደቡ ሰዎች ተዘጋጁ::

የሔርማንስቡርግ ሚስዮን ማኅበር ሚስዮናውያን በመርከብ ተጉዘው በዛሬዋ ኬንያ በኩል ወደ ኦሮሞ ሕዝብ ለመድረስ ያደረጉት ሙከራ ሁለት ጊዜ ተደናቀፈ:: ከሰባ (70) ዓመት በኋላ በ1928 ዓ.ም የጀርመን የወንጌል መልእክተኞች በወለጋ አይራ የወንጌል ሥራ እንዲሁም የትምህርትና የጤና አጠባበቅ ሥራ ጀመሩ::

ከቄስ ሉዊ ሐርምስ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው የስዊድን ወንጌላውያን ኅብረት «የስዊድን ወንጌላዊት ማስዮንን» በማቋቋም በ1966 ዓ.ም ሦስት የወንጌል ሚስዮናውያንን በምፅዋ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ላኩ:: ትግራይን አቋርጠው ወደ ኦሮሞ ምድር መሄድ ስለተከለከሉ ከምፅዋ ወደብ አቅራቢያ እምኩሉ በተባለ ሥፍራ ጊዜያዊ የሚስዮን ጣቢያ ከፍተው ማስተማር ጀመሩ:: ኦነሲሞስ ነሲብ (ሂካ አዋጅ) ትምህርቱን ስዊድን አገር ፈጽሞ በ1881 ዓ.ም ወደ ምፅዋ እምኩሉ ተመልሶ ነበር:: ሚስዮኑ ኦነሲሞስ የነበረበት አምስት ሰዎች ያሉት አንድ ቡድን አባሎች በሸዋ በኩል ወደ ጅማና ኢሉባቡር ለመዝለቅ ቢሞክሩም ከሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ፈቃድ ባለማግኘታቸው ምክንያት ወደ እምኩሉ ተመለሱ:: የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን ጥረት ባለመሳካቱ ሌሎች ዘዴዎችን መፈለግ ጀመሩ:: ሚስዮናውያኑ ከምፅዋ አካባቢ ወደ ሐማሴን ወጥተው በ1890 ዓ.ም አስመራ ላይ ሰፈሩ:: በዚህ ወቅት አንድ የኦርቶዶክስ ካህን የነበረ የሐማሴን ሰው ለወንጌል ስብከት ወደ ኦሮሞ አገር መሄድ እንዲፈቀድለት ለሚስዮኑ መሪዎች ጥያቄ አቀረበ:: እርሱም ቄስ ገብረ ኤዎስጣቴዎስ ዘሚካኤል (በሕዝብ አጠራር ገብረ ስታቴስ) ይባል ነበር:: ገብረ ስታቴስ የኦሮሞን ቋንቋ ከኦነሲሞስ ይማር ነበር:: ጥያቄውም ተቀባይነት አገኘ:: ከቄስ ገብረስታቴስ ጋር ባለቤቱ ወ/ሮ ጎዕመሽ ወልደ ሚካኤል፣ አቶ ዳንኤል ደቦላ፣ ባለቤቱ ወ/ሮ ጥሩ ገብሬና ወንጌላዊ የሆነው መነኩሴ አባ ገብረ እግዚአብሔር ኮከበወርቅ የአድዋ ጦርነት በተደረገ በዓመቱ በየካቲት 1897 ዓ.ም. ከአስመራ ተነሡ::

ቄስ ገብረ ስታቴስና መልእክተኞቹ በሚስዮኑ መሪዎች መመሪያ መሠረት አስቀድመው ወንጌላዊ ንጉሤ ጣሹን ለመርዳት ወደ ጅማ ሄደው ነበር:: በሡልጣን አባ ጅፋር ትእዛዝ መሠረት ንጉሤ ጣሹ ከተከለለለት መሬት ውጪ ወንጌል መስበክ ስላልተፈቀደለት ሀገሩ ለወንጌል አገልግሎት አስቸጋሪ መስሎ ስለታያቸው ዳንኤል ደበላ እና ቄስ ገብረ ስታቴስ በመመካከር ሌላ ሀገር ለመሄድ በተስማሙት መሠረት ወደ ወሎ ተጓዙ:: ገብረ ስታቴስና ጎዕመሽ ነቀምቴ እንደ ደረሱ ከፊታውራሪ ዲባባ ጋር ወደ ቦጂ ተጉዘው በታኅሣሥ ወር 1898 ዓ.ም. የዲባባ መኖሪያ ከነበረው ኮረብታ ደረሱ:: በዚህ ሁኔታ ቦጂ ወለጋ በመጀመሪያ የምሥራች ወንጌል በኢትዮጵያውያን የተሰበከበትና ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስም የተወጠነችበት ሥፍራ ሆነ::

በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ኖርዌጅያን ሉተራን ሚስዮን ያሉ ሚስዮናውያን ድርጅቶች በኢትዮጵያ በተለያዩ ሥፍራዎች የወንጌል ሥራን ጀመሩ:: የኖርዌጂያን ሉተራን ሚስዮን በኢትዮጵያ ለ60 ዓመታት ያገለገለ ሲሆን በደቡብ ኢትዮጵያ አዲስ ሥራ ለመጀመር በሚስዮኑ ምክር ቤት የጸደቀው በሚያዝያ 1 ቀን 1948 ዓ.ም. ነበር:: የሥራ ፈቃድ ታኅሣሥ 7 ቀን 1949 ዓ.ም. ከተገኘ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት ለንጉሡ በትምህርት፣ በጤና ዘርፍ ኅብረተ ሰቡን እንደሚያገለግሉ ቃል በገቡት መሠረት በይርጋዓለም የሚገኘውን የድሮ የኢጣሊያን ሆስፒታል በ1949 ዓ.ም. ለሚስዮኑ ሲሰጥ በተመሳሳይ ሁኔታ በነገሌም ያለውን ሆስፒታል ሚስዮኑ ለመረከብ ተስማማ:: በተጨማሪም አንድ አዲስ ሆስፒታል በጊዶሌ ሊጀመር ሌሎች ክሊኒኮች በየጣቢያው ተከፈቱ፣ የጤና ረዳቶችና የነርሶች ሥልጠና ተጀመረ:: ሁለት የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ተጀመሩ::

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የወንጌል አገልግሎት በኢትዮጵያ መስፋፋት ጀመረ፡፡ የክርስቶስ የማዳን ወንጌል ከተሰበከ በኋላ አንዲት ብሔራዊት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሳትመሠረት ከ40 ዓመት በላይ ማለፉን እላይ ከተመለከተው ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

**የአንዲት ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን መቋቋም**

በሉተራውያን ሚስዮናውያንና አገር በቀል በሆኑት የወንጌል አገልጋዮች ጥረት በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያና በሰሜን ኢትዮጵያ የተቋቋሙት ማኅበራት ምእመናን አንዲት ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያንን ለማቋቋም የተሰበሰቡት በሚያዚያ ወር 1958 ዓ.ም. ነበር፡፡ የተሰበሰቡትም በአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ማኅበረ ምእመናን ሲሆን 20 ተሳታፊች የተወከሉበት ጉባኤ ነበር፡፡

በዚሁ ስብሰባ ላይ በዶ/ር ሄርበርት ሺፈርና በቄስ ማንፍሬድ ሉንድግሬን የተዘጋጀ የቤተ ክርስቲያኒቱ ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የቀረበ ሲሆን ከግምቢ አውራጃ ከመጡት 6ቱ የስብሰባው ተሳታፊዎች በስተቀር ሁሉም የቀረበውን ረቂቅ ደንብና ውስጠ ደንብ መቀበላቸውን በፊርማቸው አረጋግጠው ነበር፡፡ ነገር ግን አብዛኛው የምእመናን ቁጥር የሚገኘው በግምቢ አውራጃ ስለነበር 6ቱ ተወካዮች የወከሏቸውን ምእመናን ስምምነት ሳይጠይቁ መፈረም ባለመቻላቸው ምክንያት ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም በጥር ወር 1959 ዓ.ም. ሌላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ተወሰነ፡፡ ነገር ግን ጉባኤው ቀጠሮውን ከሰጠ በኋላ ሳይበተን ቄስ ባድማ ያለው ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት በብሔራዊ ደረጃ የምትቋቋመው ቤተ ክርስቲያን ስም «የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ» እንዲሆን ጉባኤተኞች ተስማሙ፡፡

ጥር 24 ቀን 1959 ዓ.ም ከአዲስ አበባ፣ ከዓድዋ፣ ከደሴ፣ ከነቀምት፣ ከግምቢ አውራጃና ከሲዳሞ የመጡት መልእክተኞች ከሚስዮናውያን ጋር በአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ማኅበረ ምእመን ተሰበሰቡ፡፡ ከግምቢ አውራጃ የተወከሉ የጉባኤው ተሳታፊዎች በዚህኛው ጉባኤ ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱን ደንብና ውስጠ ደንብ መቀበላቸውን በፊርማቸው አረጋገጡ፡፡ ይህም ስብሰባ «የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ 1ኛ ዓቢይ ጉባኤ» ተባለ፡፡ በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ብዛት 20000 ነበር፡፡

በ1ኛው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓቢይ ጉባኤ ላይ በተደረገው ምርጫ መሠረት፡-

| | |
|---|---|
| አቶ አማኑኤል ገብረ ሥላሴ | ፕሬዚደንት |
| ዶ/ር ሄርበርት ሺፈር | ምክትል ፕሬዚደንት |
| ሑስ ማንፍሬድ ሉንድግሬን | ገንዘብ ያዥ |
| አቶ ሐጎስ ለገሠ | ዋና ጸሐፊ |
| አቶ ገብረአብ ቢያድግልኝ | ረዳት ዋና ጸሐፊ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ |

በአንደኛው ዓቢይ ጉባኤ ላይ የተሳተፉት መልእክተኞች 25 ሲሆኑ ከስዊድን ሚስዮን ቢቪ ደግሞ ሦስት እንግዶች ተገኝተው ነበር፡፡ በ20 ሺህ ምእመናን የዛሬ 50 ዓመት ገደማ በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመችው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜ ከ4.6 ሚሊዮን በላይ አባል ምእመናን ያሉአት ሲሆን ብዙ ብሔር ብሔረ ሰቦችንና ሕዝቦችን ያቀፈችና የምታገለግል ቤተ ክርስቲያን ነች፡፡

## የመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ መተርጎም

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ የተተረጎመው ከዛሬ 110 ዓመት ገደማ በፊት ነበር፡፡ ዶክተር ሎረን ኤፍ ብሊዚ እንደ ጻፉት የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኦሮሞኛ የተተረጎመው በማዕከላዊ ኦሮሚያ ይኖር በነበረ በርክ በተባለ የኦሮሞ ተወላጅና በሚስዮናዊ ዮሐን ክራፍ ሲሆን የታተመውም በ1842 ዓ.ም. ነበር፡፡

በምዕራብ ኢትዮጵያ በኢሉባቡር ሁሩሙ የተወለደው ኦነሲሞስ ነሲብ (ሂካ አዋጅ) በአራት ዓመት ዕድሜው አባቱ በሞት ከተለዩት በኋላ አደጋ ጣይ ጎሳዎች ከእናቱ ሰርቀውት ባሪያ አደረጉት፡፡ ስሙ ከሂካ ወደ ኦነሲሞስ የተቀየረው በኦክቶበር 1870 ዓ.ም ሙንዚንገር ነፃ አውጥቶት በነበረ ጊዜ ነው፡፡

ኦነሲሞስ ነሲብ የላቀ አእምሮ ተሰጥዖ እንደ ታደለች ከሚነገርላት ከአስቴር ገኖ ተገቢውን እገዛ እያገኘ የመጀመሪያውን የአዲስ ኪዳን ረቂቅ በኦሮምኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በ1893 በእምኩሉ የታተመ ሲሆን የመጀመሪያው ብሉይ ኪዳን ትርጉም በጁን 1897 ዓ.ም ተጠናቀቀ፡፡ የሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ኅትመትም በቅዱስ ክርሾና ስዊዘርላንድ ባለ ማተሚያ ቤት በጁን 1899 ዓ.ም ተፈጸመ፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ቀለል ባለ ቋንቋ የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ እስካሳተመበት እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ የኦነሲሞስ ትርጉም ከዘጠና ዓመት በላይ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

## የቤተ ክርስቲያኒቷ ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎቶች

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በብሔራዊ ደረጃ ከመቋቋሟ ከ50 ዓመታት በፊት እና በብሔራዊ ደረጃ ከተቋቋመች በኋላ ጭምር በኢትዮጵያ ውስጥ ከወንጌል ሥራ በተጓዳኝ የተለያዩ የልማትና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ስታበረክት ቆይታለች፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቷ እንድትቋቋም አስተዋጽኦ ያደረጉ ሚስዮናውያን በወቅቱ ከነበረው የአገሪቱ አስተዳደር ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረት በተለይም በትምህርትና በጤና ዘርፍ የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተጨማሪም ምእመናን በእምነት እንዲጸኑና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያነቡ በማሰብ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶችን እንድትከፍትና ታዋቂ የነበረውን የምሥራች ድምፅ የመሠረተ ትምህርት በ1962 ዓ.ም እንድትጀምር ሆኗል፡፡ የምሥራች ድምፅ መሠረተ ትምህርት ለመሠረታዊ የሂሳብ ዕውቀት፣ በማንበብና በመጻፍ፣ በመሠረታዊ የኑሮ ዘዴ እና የኢኮኖሚ እድገት ዙሪያ ክህሎትን ማስጨበጥ ዋናው ዓላማ ነበር፡፡ የመሠረተ ትምህርት በ30 ዓመት ታሪኩ ከ1 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ከመሐይምነት ቀንበር ነፃ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ መሐይምነትን ለማጥፋት ባደረገው አስተዋጽኦ የዩኔስኮ ሽልማት አግኝቷል፡፡

የምሥራች ድምፅ መሠረተ ትምህርት ከመጀመሩ አስቀድሞ የምሥራች ድምፅ ሥነ ጽሑፍ ድርጅት ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊና ትምህርታዊ የሆኑ መጻሕፍትን በማዘጋጀት፣ በማሳተምና በማሰራጨት በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ ጉልህ ስፍራ ይዞ ነበር፡፡ ከመሠረተ ትምህርት ጋር የነበረው መደጋገፍም የሚናቅ አልነበረም፡፡

ቤተ ክርስቲያን እስከ ቅርብ ዓመታት 34 የ1ኛ ደረጃ፤ 10 መለስተኛ ደረጃ እና ሦስት (3) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአገሪቱ ደቡብ ምዕራብ ሠርታ ለደርግ ካስረከበቻቸው ሁለት ሌሎች አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር 49 ት/ቤቶችን በመሥራት ሕዝቡን ተጠቃሚ አድርጋለች፡፡ ከእነዚህም ሌላ በደርግ አስተዳደር የተወረሰ በደብረ ዘይት (ቢሾፍቱ) የሚገኝ አንድ ኮሌጅ የሚጠቀስ ሲሆን በዓድዋ፣ በይርጋዓለም እና በነጆ ሦስት የመምህራን ማሠልጠኛ ማዕከላት ነበሯት፡፡ በተጨማሪም የአርባ ምንጭ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት አሁንም በቤተ ክርስቲያኒቱ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ በነጆና በበደሌ የነበሩ ሌሎች የቴክኒክና የሙያ ት/ቤቶች በደርግ መንግሥት ተወርሰዋል፡፡

ከመደበኛ ት/ቤቶች በተጨማሪም በጊምቢ ማየት የተሳናቸው ት/ቤት ለአያሌ ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በሆሳዕና ከተማ ደግሞ በ1981 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ መስማት የተሳናቸው ት/ቤት የተመሠረተ ሲሆን ዋና ዓላማው መስማት ለተሳናቸው ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል የአካዳሚ ትምህርት መስጠትና ለሁለት ዓመት ደግሞ የሙያ ትምህርቶችን መስጠት ነበር፡፡

በሌላ በኩል የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለባቸው ዜጎች (Mentally challenged people) ማዕከል በአዲስ አበባ በ1986 ዓ.ም ተጀመረ፡፡ ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት በመካኒሳ አካባቢ ከ300 በላይ ልጆችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ት/ቤቶችን ከማስፋፋት በተጨማሪ ገጠርን ማዕከል ያደረጉ ሌሎች የልማት ሥራዎችን ስታከናውን ቆይታለች፡፡ ለምሳሌ፡- በትግራይ የሚገኘው የሰለክላካ ፕሮጀክት፣ በወለጋ የሚገኘው የሔና ፕሮጀክት፣ እና በወሎ ያለው የውጫሌ ፕሮጀክት ለኅብረተ ሰቡ ልማት ያበረከቱት አስተዋጽዖ ከፍተኛ የነበረ ሲሆን፣ በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያኒቱ የልማት ፕሮግራም አማካይነት በወንዶገነት እና በጨሊያ ለገበሬዎች የሚሰጠው ሥልጠና የሚያበረታታ ውጤት አስገኝቷል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በጤናው ዘርፍም የላቀ አስተዋጽዖ ያበረከተች ሲሆን፣ ለምሳሌ የመጀመሪያውን ሆስፒታል (አሁን ፓስተር ኢንስቲቲዩት የሚባለውን) ከአሜሪካ ፕሪስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር ከመጀመሯ ባሻገር በወልዲያ፣ በአይራ፣ በደምቢዶሎ፣ በይርጋዓለም፣ በነገሌ ቦረና፣ እንዲሁም በጊዶሌ ያሉት ሆስፒታሎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የቤተ ክርስቲያኒቱ ተባባሪ የሆነው የዓለም ሉተራን ፌዴሬሽዮን በኢትዮጵያ ታዋቂና ቀደምት የነበረውን በተለያዩ ፕሮግራሞች አማካይነት ኅብረተ ሰቡን በማንቃትና በማስተማር ከፍተኛ ድርሻ ያበረከተውን የብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ አቋቋመ፡፡ በሥሩ ከነበሩት ስቱዲዮዎች አንዱ የምሥራች ድምፅ ራዲዮ ስቱዲዮ ነበር፡፡

በዚህ ስቱዲዮ አማካይነት ቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፕሮግራሞችን እያዘጋጀች ኅብረተ ሰቡን በማስተማር ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥታለች፡፡ በ1969 ዓ.ም. ብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያና የምሥራች ድምፅ ራዲዮ ስቱዲዮ ከተወረሱ በኋላ ሥራው በውጪ እንዲቀጥል ተደርጎ ለኢትዮጵያ አድማጮች አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶአል፡፡ እ.ኢ.አ. በ1992 በስደት ላይ የነበረው የራዲዮ አገልግሎት፣ በአገር ውስጥ የነበሩት የኦዲዮ ቪዥዋልና የሥነ ጽሑፍ አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የምሥራች ድምፅ የመገናኛ ዘዴዎች አገልግሎት ሥር እንደ ገና ተደራጅተውና ተጠናክረው በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በአገሪቱ ከመንፈሳዊ አገልግሎቶቿ ባሻገር ለኅብረተ ሰቡ ፋይዳ ያላቸውን የልማትና የማኅበራዊ ሥራዎችን በከፍተኛ ደረጃ ብታከናውንም ቀደም ሲል በነበሩት የአገሪቱ ሥርዓቶች በነፃነት የማምለክ መብት ከመገፈፏ የተነሣ በአደባባዮች ተሰብስቦ ማምለክ የማይታሰብ ጉዳይ ነበር፡፡ በተለይም በደርግ አገዛዝ ዘመን የቤተ ክርስቲያኒቷ የቀድሞ ጠቅላይ ጸሐፊ ቄስ ጉዲና ቱምሳን ጨምሮ ብዙዎች ሞተዋል፣ የደረሱበት ጠፍቷል፣ ሌሎችም ለእስራት፣ ለእንግልት ተዳርገዋል፣ ከአገር እስከ መሰደድም ደርሰዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቷ ላይ አንዣቦ የነበረው ስደት የልማትና የማኅበራዊ ሥራዎቿ ከመወረሳቸው የተነሣ የቤተ ክርስቲያኒቷ የልማት ሥራዎች በከፍተኛ

ደረጃ እንዲቀንሱ ምክንያት ሆነው ነበር። ነገር ግን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የገሃነም ደጆች ሊቋቋሚት አይችሉምና እያበራች ትኖራለች። አሜን።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በየዓመቱ በአማካይ ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ በማፍሰስ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ከ6 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን ታንቀሳቅሳለች።

**ዋቢ መጻሕፍት**


Aren, Gustav, (1999) *Envoys of the Gospel in Ethiopia, in the steps of The Evangelical Pioneer*, EFS forlaget, Stockholm, Sweden

Emmanuel Abraham, (1995) *Reminiscence of my Life*, LUNDE forlag, Oslo, Norway

Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus Development and Social Service Commission, (2006) Annual Report 2006, Central Printing Press, Addis Ababa

**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመችበት 40ኛ ዓመት-ታሪክና አገልግሎቷ በአጭሩ፣ (1991) ልዩ መጽሔት**